# ጠቃሚ መረጃ

## የጥቃት ሰለባዎችን ማሳተፍ

## ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ትንኮሳ (SEAH)

ይህ ጽሑፍ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ (SEAH) ሰለባዎችን በፖሊሲ ማውጣት ሂደት ውስጥ ስናሳትፍ መገንዘብ ያለብንን ጥሩ ልምድ የሚያስረዳ ፈጣን ማጣቀሻ ነው፡፡[1] ድርጅቶች ከጥቃት ሰለባዎች ጋር ሲሠሩ ሊጠይቋቸው የሚገቡትን ቁልፍ ነጥቦችን እና ጥያቄዎችን በዝርዝር ያስቀምጣል።

የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና የወሲባዊ ትንኮሳ (SEAH) ሰለባዎች ስለ ጉዳዩ ፖሊሲን ስናወጣ ጠቃሚ አስተዋፅዖ ማድረግ ይችላሉ። ሆኖም ትርጉም ያለው ተሳትፎ ይኖራቸው ዘንድ ፖሊሲ አውጪዎች ተጨማሪ ጉዳትን ሳያስከትሉ በትክክለኛ እና ኃላፊነት በተሞላ ሁኔታ የጥቃት ሰለባዎችን ድምፅ መስማታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ ነው።

### የጥቃት ሰለባዎች ለምን ይሳተፋሉ?

- ✓ ድርጅቶች የጥቃት ሰለባዎችን ዕይታ እና ልምዶች በቁም ነገር እንዲመለከቱ የሥነ ምግባር እና የሞራል ኃላፊነት አለባቸው።
- ✓ የጥቃት ሰለባዎች ካሳለፉት ልምድ የተነሣ ከማንም ይልቅ የሚሠራውን እና የማይሠራውን አሳምረውያውቃሉ።
- ✓ በፖሊሲ እና የለውጥ ሂደቱ መካተታቸው የጥቃት ሰለባዎች ከሁኔታቸው እንዲያገግሙ ከመርዳቱም ባሻገር ዋጋ እንዳላቸው እንዲሰማቸው ሊያደርግ ይችላል።
- ✓ የጥቃት ሰለባዎችን ማሳተፍ ሥራው ተገቢ እና ውጤታማ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይችላል።
- ✓ ሠራተኞች እና ድርጅቶች የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ከጥቃት ሰለባዎች ዕይታ አንጻር ሲረዱ ሚናቸውን በተሻለ መልኩ ይወጣሉ።

### የጥቃት ሰለባዎች ለምን አይሳተፉም?

- ✕ የጥቃት ሰለባዎች አሁንም በበዳያቸው (በበዳዮቻቸው) ለሚደርስባቸው አደጋ/ስጋት የተጋለጡ ከሆኑ
- ✕ ድርጅትዎ በተሳትፎው ወቅትም ሆነ ከዛ በኋላ የጥቃት ሰለባዎችንና የጠቋሚዎችን ደኅንነት ለመጠበቅ ትክክለኛ ፖሊሲ እና አሠራር ከሌለው
- ✕ ተሳትፏቸው የጥቃት ሰለባዎችን የሚጎዳ ከሆነ ወይም ለበዳዮች፣ ለማኅበረሰቡ ወይም ለመንግሥት ጥቃት የሚያጋልጣቸው ከሆነ (ለምሳሌ፣በመናገራቸው ምክንያት እንደ እስራት ወይም የሙብት ማጣትን ሊያጋጥማቸው የሚችል ከሆነ)
- ✕ ተሳትፎው ድርጅቱን ለመጥቀም ብቻ እንጂ የጥቃት ሰለባዎችን ካልሆነ
- ✕ ድርጅትዎ በጥቃት ሰለባዎቹ የተሰጡትን ምክሮች ለመተግበር ፍላጎት ከሌለው

**ጠቃሚ ትርጓሜዎች፡-**

**የጥቃት ሰለባዎች -ተኮር አቀራረብ**:- ለአደጋ በተለይም ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖችን ጨምሮ መከላከልና እና ምላሾች አድልዎ የሌለባቸው፤ **የጥቃት ሰለባዎችን የሚያከብር** እና **መብቶቻቸውን**፣ **ፍላጎቶቻቸውን** እና **መሻቶቻቸውን የሚያስቀድም** መሆኑን ማረጋገጥ[2]

**የጥቃት ሰለባዎች መር አቀራረብ**:- የጥቃት ሰለባዎች በሕይወታቸው ከደረሰባቸው እና ከተቋቋሙት መጎሳቆል እና/ወይም ብዝበዛ ወጥተው በራሳቸው ሕይወት እና በትልቁ እንቅስቃሴ ውስጥ የመሪነት ሚናን እንዲይዙ የሚያስታጥቅ እና ኃይል የሚሰጥ አቀራረብ ነው።[3]

**የስሜት ቀውስን ያገናዘበ አቀራረብ፡-** የስሜት ቀውስ የሚያስከትለውን ሰፊ ተጽዕኖ የሚገነዘብ እና ለማገገም ሊረዱ የሚችሉ መንገዶችን የሚረዳ አቀራረብ ነው። ይህ የስሜት ቀውስ ምልክቶችን ለይቶ ማወቅን ያካትታል፤ ስለስሜት ቀውስ ያሉ ዕውቀቶችን በፖሊሲዎች፣ አሠራሮች እና ልምምዶች ላይ ሙሉ በሙሉ በማዋሃድ እና እንደገና ሊገጥም የሚችል መጎዳትን ለመከላከል በንቃት ማቀድን ይጨምራል።[4]

ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ የቀረበው ድርጅቶች የጥቃት ሰለባዎችን ተሳትፎ ሲያቅዱ ለመምራት ታስቦ ነው። ይህ ሰፊ ዝርዝር አይደለም ነገር ግን የጥቃት ሰለባዎች ተሳትፎ ምን እንደሚያካትት ለማስጨበጥ ነው።

**ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተደራሽ የሆነ አካባቢን ይፍጠሩ**



**ለጥቃት ሰለባዎችና ለጠቋሚዎች የደኅንነት ጥበቃ እርምጃዎች መኖራቸውን ያረጋግጡ።** የደህንነት መጠበቂያ ፖሊሲዎችዎ እና አሠራሮችዎ ወቅታዊ እና ጠቃሚ ናቸውን? በተሳትፎ ጊዜ ወይም  መረጃ ይፋከተደረገ በኋላየጥቃት ሰለባዎችን የሚደግፍ ሂደት አለዎት?

**የደህንነት ዕቅድ መተገበሩን ያረጋግጡ።** የተሳትፎ ስጋት ግምገማ አካሂደዋልን? በተሳትፎ ጊዜ እና በኋላ የግል የደህንነት ዕቅዶችን ለማዳበር ከጥቃት ሰለባዎችእና ሠራተኞች/አመቻቾች ጋር ሠርተዋል?

**በምክክሩ ወቅት የጥቃት ሰለባዎች በማንኛውም ነገር ከተጎዱ ድጋፍ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ።** ምን ዓይነት አገልግሎቶች ያስፈልጋሉ? ከማን ጋር መገናኘት ወይም አብረው መሳተፍ ይፈልጋሉ? ለልጆች ልዩ እርምጃዎችን ከግምት አስገብተዋል? አገልግሎቶች እንዴት እንደሚከፈሉ አስበዋል?

**አካባቢው ተደራሽ እና አካታች መሆኑን ያረጋግጡ።** ከተለያዩ አካባቢዎች ወይም አስተዳደግ የመጡ የጥቃት ሰለባዎችን እንዴት ያካትታሉ? የጥቃት ሰለባዎች ወደ ስብሰባው ቦታ መጓጓዣ እንዲያገኙ እንዴት እየደገፉ ነው? ወላጆችን በሕፃናት እንክብካቤ፣ የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦችን ወይም ሌሎች ቡድኖች እንዲሳተፉ  እንዴት ይደግፋሉ?

**ምስጢራዊነት እና ማንነትን መደበቅ ያረጋግጡ።** የጥቃት ሰለባዎች በተሳትፏቸው ተለይተው በመታወቅ ለአደጋ ተጋልጠዋል? ማንኛውንም ሥራ እንዳይታወቁ በማድረግ እና ተለይተው እንዲታወቁ የሚያደርጉ መለያ ነገሮችን በማስወገድ ላይ ነዎት?

**በአስተዋይነት፣ በግንዛቤ እና ሀሳብ በመስጠት  መሳተፍ፡፡**



**ሂደቶች በሙሉ  በጥቃት ሰለባዎች የሚመሩ እና የተነደፉ መሆን አለባቸው።** የጥቃትሰለባዎች ተጨማሪ ጉዳት እንዳያስከትሉ አድርገው ተሳትፎን፣  ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን በመቀየስ እና በመምራት ረገድ እንዴት ቀዳሚ ሚና  ሊኖራቸው እንደሚችል አስበው ያውቃሉ?  የትኞቹ መንገዶች ለእነሱ የተሻለ እንደሚያገለግሉ የጥቃት ሰለባዎችን ጠይቀዋል?

**ጥቅም ላይ ለሚውሉ ማንኛውም ተሳትፎ እና ምስሎች፣ ጥቅሶች ወይም የጽሑፍ ሥራ የተረጋገጠ** በዕውቀት ላይ የተመሠረተ **ፈቃድ/ስምምነት መገኘቱን ያረጋግጡ።** ተሳትፎ ምንን እንደሚያካትት ወይም ምን እንደሚያስከትል፣ ስምምነትን ሲባል ምን ማለት እንደሆነ የጥቃት ሰለባው/ዋ በትክክል በሚገባው/ት መንገድ አስረድተዋል? በማንኛውም ጊዜ ተሳትፎን ማቆም እንደሚቻል አብራርተውላቸዋል? ማናቸውንም ምስሎች ፣ ጥቅሶች ወይም የጽሑፍ ሥራዎች እንዴት ተግባር ላይ እንደሚውሉ እና ማን ሊመለከታቸው እንደሚችል አብራርተውላቸዋል? ማንኛውም ሥራ በኢንተርኔት መስመር ወይም  ለሕዝብ ክፍት ሰነድ ሆኖ ይታተማል?

**ተስፋን በተመለከተ ግልፅ ፣ እውነተኛ እና ተጨባጭ ይሁኑ።** እጅዎ ላይ ባሉት ግብዓቶች እና የጊዜ ገደብ ውስጥ ምንን ለማሳካት እንደሚችሉ ተጨባጭ ነዎት? ከተሳትፎው ስለሚጠበቀው ውጤት/ነገር  ግልፅ ነገር  አለዎት?  የጥቃት ሰለባው/ዋ ስለ እርስዎ ሚና እና ማንኛውም ገደቦች በግልጽ ተረድተዋል? ስልክ እደውላለሁ፣ የጽሑፍ መልዕክት እልካለሁ ወይም መረጃ እልካለሁ ብለው ቃል ገብተዋል? ካሉ፣ ማድረግዎን ያረጋግጡ።

**ከሂደቱ በፊት እና በኋላ ያሉት ግንኙነቶች ግልፅ እና ወዳጃዊ መሆን አለባቸው።** የጥቃት ሰለባዎቹ ጋር ያለው ግንኙነቶችተመችቷቸዋል? ምን እንደሚሆን እና  ሌላ ክትትል ማስፈለጉን ሂደቱን አብራርተውላቸዋል ? ድምፅዎ እና የሰውነት እንቅስቃሴዎ (ቋንቋ) ምቾት የሚሰጣቸውነው? ጭፍን ጥላቻዎትዎ እና አድልዎችዎ ላይ አስበውበታል እንዲሁም ይህ ከግለሰቦች ጋር ያለዎት ግንኙነት ላይ እንዴት ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ተገንዝበዋል?

**የጥቃት ሰለባዎቹ እንዴት መሳተፍ እንደሚፈልጉ ለመምረጥ እንዲችሉ የተለያዩ አማራጮችን ያቅርቡ።** የጥቃት ሰለባዎቹ የሚያሳትፉ የተለያዩ መንገዶችን (የጽሑፍ ሥራ፣ የድምጽ (ኦዲዮ)፣ ኪነ ጥበብ ላይ የተመሠረተ ወዘተ) አስበዋል? የጥቃት ሰለባው/ዋ ሊኖሩት/ ሯት የሚችሉ የተለያዩ አማራጮች እና የተለያዩ ሚናዎች ወይም ግብዓት እንዳለ ያውቃል/ታውቃለች?

**ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች፣ ገንዘብ፣ ሠራተኞች እና ሌሎች ንብረቶችን ማቅረብ እና እንደሁኔታው የሚለዋወጥ ማድረግ።**



**ከወሲባዊ ጥቃት የተረፉ ግለሰቦችን ለማሳተፍ ሠራተኞች እና ጊዜ ምደባን በተመለከተ እርግጠኛ ይሁኑ።** በተለይ ከልጆች እና ከአካል ጉዳተኞች ጋር ሲሰሩ ተሳትፎውን ለመደገፍ  ብቃት ያላቸው በቂ ሠራተኞች አሉዎት? ያልተጠበቁ ለውጦች  ቢከሰቱ ተጠባባቂ ዕቅድ አካተዋል? ለምሳሌ የጥቃት ሰለባው/ዋ መጨረሻ ደቂቃ ላይ አልሳተፍም ቢል/ብትል መልሶ/ሳ መሳተፍ ቢፈልግ/ብትፈልግስ? ክፍለ ጊዜውን እንደገና ማስያዝ/መቅጠር ይችላሉ?

**የተሳትፎ ወጪን ከግምት ያስገቡ።** ለተሳታፊዎች ምግብ ይሰጣሉ? የዝግጅት ቦታ ወጪዎች አሉ? ለአጭር እረፍት ወይም ለቡድን ውይይቶች ቦታ ያስፈልጉዎታል? አስተርጓሚዎች ያስፈልጉዎታል?

**የጥቃት ሰለባዎቹ ላካፈሉን ዕውቀት በገንዘብ ይካሱ።** የጥቃት ሰለባዎቹ ለሚያጠፉት ጊዜ እየተከፈሉ ነው? ማንኛውንም የጉዞ እና የማረፊያ ቦታ ወጪዎችን ማካካሻ ገንዘብ እየከፈሉ ነው (የጥቃት ሰለባዎቹ ወደ ስብሰባው ቦታ ለመድረስ ይህንን በቅድሚያ ሊያስፈልጋቸው ይችላል)? ለሕፃናት መዋያ ወይም ለሕፃናት መዋያ ወጪዎችን እየሰጡ ነው?

